# ካፒታሊዝም ግን በጠረባ ቡድን አይገነባም

ታሪኩ አባዳማ ሰኔ 2001

ኢዝም ኢዝም ሲባል ብዙ ትውስታ ይጭራል። በደርግ ዘመን ካንድ የገጠር ከተማ ለካድሬነት ስልጠና ተመልምሎ የመጣ ጮሌ ስለ ሶሻሊዝም የቀሰመውን ከቀየው ተመልሶ ሲተነትን ያለውን ላስታውሳችሁ:-

“... ሶሻሊዝም  የመጣው ከሁለት ቃላት ነው ... ሶሻል እና ዝም ከሚለው። ‘ሶሻል ማለት ህብረት’ ሲሆን ‘ዝም ደግሞ ያው ዝም ነው’ በማለት ካድሬው ንግግሩን በመቀጠል ‘...ሶሻል እና ዝም’ አንድ ላይ ሲነበብ በንግሊዝኛ ሶሻሊዝም ወደ አማርኛ ሲመለስ ደግሞ “በህብረት ዝም” ማለት ነው’ ሲል ይህ ‘ሳይንሳዊ’ ትርጓሜ መሆኑን ጭምር አክሎ ፣ ለንቃት ተጠርተው ፣ በህብረት ዝም ብለው ሲያዳምጡ የነበሩትን አስደምሞ ሸኟቷል።

‘ግባችን እሩቅ - አላማችን ታላቅ’ በሚል መፈክር የታጀበው ይህ የደርግ ሶሻሊዝም ፣ ኮለኔሉ ‘ሩቅ’ ሳያደርሱን ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ ከቶውንም አሳብ እንዳልነበራቸው ያስነገሩበት ነበር። ታዲያ ‘ግባችን ሩቅ ነው’ ያሉት ሰውዬ አንድ ቀን ምሳ ሰዓት ላይ አውሮፕላን አስገድደው ወደ ሩቅ አገር መጥፋታቸውን ሰማን። ከድሀ መንደር ተመልምሎ የመጣው ካድሬ እንደ ምድራዊ ገነት ተመስሎ የተሰበከለት ሶሻሊዝም በኢትዮጵያ ምድር ያውም በወታደር አመራር ሊታሰብ እንደማይችል ገና ድሮ ጠንቅቆ አውቋል።

‘ማወቁን እናውቃለን - ብንናገር እናልቃለን’ ነበር ነገሩ። እናም በደርግ ዘመን - የተናገሩ እያለቁ ፣ በሰደፍ እየደቀቁ ፣ በእስር እየማቀቁ - የተረፉት ሲሰደዱ - ‘በህብረት ዝም’ ያሉ ደግሞ ከድጡ ወደ ማጡ ተንሸራተው ወያኔ ክርን ሥር ወድቀዋል -  እምምም ፣ ይቅርታ ፣ ወያኔ እጅ ወድቀናል።

ሆኖም ሲሆን - በዝምታ የሚመጣ ነፃነት አለመኖሩን ዕድሜ መስታወት ሆኖ እያስተማረን ነው።

አቦይ ስብሀት ደግሞ ቪኦኤ ላይ ቀርበው ‘እኛ (ወያኔ) የመጣነው ካፒታሊዝምን ለመገንባት ነው ፤ አንዴ ገንብተነው ስናበቃ እንከስማለን - አላማችንም ይኸው ነው’ አሉ። የወያኔ ግብ ‘ሩቅ’ መሆኑን አቦይ በፎርም ነገሩን። እናም ካፒታሊዝም በወያኔ እጅ ተገንብቶ ማብቃቱን እስኪያውጅ በትዕግስት መገዛት የኛ ፈንታ መሆኑን አቦይ ስብሀት አረዱን። ደርግ እና ወያኔ የሚለያዩበት ብዙ መሠረታዊ ነገር መኖሩን ብገነዘብም ‘ሩቅ’ የምትለዋ ነጥብ ነጥራ ስትወጣ ግን ጭፍን አምባገነኖች በባህሪያቸው ተመሳሳይ መሆናቸውን ይበልጥ ተገንዝቤያለሁ። ሶሻሊዝም በወታደር - ካፒታሊዝም በጎጥአደር - የኢትዮጵያ አበሳ ማለቂያ የለውም።

ለአቦይ ስብሀት ትንታኔ ምስጋና ይግባውና ካፒታሊዝም ተገንብቶ የሚያበቃበት ግዜ በወያኔ ተሰልቶ እየተሰራበት መሆኑን ሰማን - በአስር አመት ውስጥ በቀን ሶስት ግዜ እንደምንበላ ድሮ ጠ/ሚኒስትሩ የነገሩን አይነት መሆኑ ነው። ካስራ ስምንት አመታት በሁዋላ ዛሬም እኛን ጠኔ እና ጥይት እየፈጀን ነው - እነሱም መቀባጠራቸውን እና መግደላቸውን አላቆሙም።

አቦይ የሚናገሩትን ያውቁ እንደሁ እንጃ እንጂ ካፒታሊዝም በቆረጣ ስልት የሚጨበጥ የጎጠኛ ማላገጫ አይደለም። እንዴት ቢሉ ካፒታሊዝም በመላው ህብረተሰብ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ሁለንተናዊ ዕድገት ነው፦ ቴክኖሎጂ ፣ ፖለቲካ ፣ የኑሮ ደረጃ ፣ የአስተሳሰብ ደረጃ ፣ ሰብአዊ መብት ...ወዘተ።

እኔ በበኩሌ - መሬት በሞፈር እየታረሰ ፣ ህብረተሰብ በጎጥ ተሸንሽኖ በጠመንጃ እየታመሰ ባለበት አገር ካፒታሊዝም የሚታለም አይደለም እላለሁ።ይህ አቋሜ ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ የወያኔ ‘ካፒታሊዝም ምሥረታ ፍፃሜ’ አዋጅ እስከሚወጣ ቆሜ መጠበቅ የለብኝም። ‘ሁሉም ዘብ ይቁም በቦታው’ ነው ያለው የፈረንሳዩ ሶሻሊስት ቀማሪ? ሞኝህን ፈልግ በሉት!!

ካፒታሊዝም ጠንካራ ብሔራዊ አንድነት ያለው የአገር ባለቤትነት ስሜት የሰረፀበት ሕዝብ የሚገነባው ሥርዓት ነው። ዜጎች በነፃ በመረጡት ያገራቸው ክልል የመኖር እና የመሥራት መብት ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ/አገራዊ ስሜት በጠንካራ የህግ ዋስትና ላይ መረጋገጥን የግድ ይላል።

ካፒታሊዝም በሽፍትነት ባንክ ዘርፎ መርከብ መግዛት ፣ ሬስቶራንት መክፈት ወይም ኮንዶ እንግሊዝ አገር ገዝቶ እንደ ማከራየት ቀላል ጉዳይ አይደለም። ካፒታሊዝም በዳንስ ቤት ግንባታ ወይም በኮንዶሚንየም ችርቻሮ የሚገለፅ ሥርዓትም አይደለም።

አንድ የፖለቲካ ሥርዓት በአመፅ ሊወገድ ይችላል - ካፒታሊዝም የሚገነባው ግን በሁለንተናዊ የሳይንስ ዕድገት ብቻ ነው። ሳይንስ ደግሞ የተረጋጋ ሰላም በሰፈነበት ህብረተሰብ ውስጥ የተኮተኮተ አይምሮ ጭማቂ ውጤት ነው። የተረጋጋ አይምሮ ከሰላም ፣ ከነፃ ውይይት ፣ ከነፃ ምርጫ ፣ ከነፃ የፅሁፍ ነፃነት ፣ ከነፃ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ አደረጃጀት ይመነጫል። ግርግር እና ወከባ በሰፈነበት የወያኔ ሥርዓት ሳይንስ እና ካፒታሊዝም ዘበት ነው። ታንክ እና መትረየስ በሚንጣጣበት ዩንቨርሲቲ ፈጠራ እና ምርምር አይኖርም።

ወያኔ ለከት ባጣ የጎጥ መከታ ሥልጣንን እና ዘረፋን ግቡ ያደረገ ፣ ባንድ  ጆምበር ቱጃር የሚቀፈቀፍበት የጠረባ ቡድን ጎጆ መሆኑን ሁሉም ያውቃል። የወያኔ ቱጃሮች በካፒታሊስት አለም ምን እየተከናወነ መሆኑን እንኳ በወጉ መረዳት የሚችሉ አይደሉም። በእጃቸው አንጠልጥለው የሚዞሩት ሞባይል ፣ የሚያሽከረክሩት ውድ መኪና የሚንደላቀቁበት ቪላ በጠረባ ተዘርፎ የተገኘ እንጂ ለዕድገት አመቺ ሁኔታ ፈጥረው በዚያ በተካበተ ጥሪት የተገኘ አለመሆኑን ከሁላችንም በላይ እነሱ ያውቁታል። ደግሞም አቦይን ጨምሮ ፣ የጠረባ ቡድን አባላት የተንደላቀቀ ህይወት መኖራቸው ንቅዘትን እንጂ ዕድገትን አያመለክትም።

ካፒታሊዝም እየነቀዘ አይፋፋም። ካፒታሊዝም ዳይናሚክ ነው - የፈጠራ እና አዳዲስ ግኝቶች ውጤት ነው።

ካፒታሊዝም በህብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ሂደት ነበር - ሂደቱ ሁዋላ ቀር እና ጎታች አስተሳሰቦችን እየጨፈለቀ የሰውን ልጅ የፈጠራ እና የአድራጊነት ብቃት እያስመሰከረ የበለፀገ ሥርዓት ነው። ሳተላይት እና ኮምፒዩተር ፣ መኪና አውሮፕላን እና ኤሌክትሪክ ሀይል ፣ ስልክ ፣ ፋክስ ኢንተርኔት …ወዘተ ተፈልስፈው የሰው ልጅ እምቅ የፈጠራ ብቃት የተመሰከረበት ሥርዓት ነው። ካፒታሊዝም ኢንቬስተር ይጠይቃል ፣ ያውም በፖለቲካ ሥርዓት እና በሕግ የበላይነት የሚመካ ልበ ሙሉ ኢንቬስተር። አንድ የፖለቲካ ቡድን ያሻውን ደንብ እና ሥርዓት እየደነገገ እና እየሻረ በሚፈጥረው ውስብስብ መሰናክል ውስጥ ታፍኖ የሚመጣ ካፒታሊዝም የለም።

ካፒታሊዝም በነፃ መተንፈስ ፣ በነፃ መወዳደር ፣ በነፃ መብለጥ ፣ በነፃ ቀድሞ መገኘት ማለት ነው። በነፃ መሪዎቹን የመረጠ ህዝብ እንደ አውሬ ታድኖ በሚፈጅበት አገር ከቶውንም ካፒታሊዝም ሊታሰብ አይችልም።

አቦይ ስብሀት ካፒታሊዝም በጠረባ ቡድን ይገነባል ነው የሚሉት ፤ ካፒታሊዝም ሴራ እና አፈና ፣ ስጋት እና መሸማቀቅ በተንሰራፋበት አስተዳዳደር ሥርዓት ውስጥ ሊያብብ ይችላል ነው የሚሉት። ህዝብ እንደ ፈረስ ተለጉሞ ያንድ ፈላጭ ቆራጭ ጎጠኛ የፖለቲካ ሀይል ያወጣውን ቀጭን ፖሊሲ ብቻ እንዲከተል በጠመንጃ አፈሙዝ ተገዶ ባለበት ሁኔታ ካፒታሊዝም ያብባል ነው አቦይ ስብሀት የሚሉት።

እኛ ደግሞ ካፒታሊዝም በፈጠራ እና በሥርዓት በሚገዛ ነፃ ውድድር የማያቋርጥ የዕድገት ሂደት ላይ የተገነባ ሥርዓት ነው ባዮች ነን። ለካፒታሊዝም ዕድገት መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች እና በሂደቱ ውስጥ እንደ አካል ሆነው የሚያንቀሳቅሱት አያሌ ጉዳዮች አሉ። መሠረታዊው የኤኮኖሚ ዕድገት ከሚደቅነው የእውቀት እና ማኔጅመንት ብቃት ጥያቄ አንስቶ በአርት ፣ ሳይንስ ፣ ፍልስፍና ብሎም መሠረታዊ የሰብአዊ መብት መረጋገጥ እና የሕግ የበላይነት ጥያቄ ጋር እጅጉን የተቆራኘ ነው እንላለን። ወያኔ ካፒታሊዝምን ይገነባል ብሎ መገመት ከእባብ እንቁላል እርግብ የመጠበቅ ያህል ነው።

እና - አቦይ እርሶ እና የርሶ ተቀፅላዎች የዘረፋችሁትን ያገር አንጡራ ሀብት የሚያስተፋ ዘመን እስኪመጣ መቀባጠሩን ትታችሁ - ተምነሽነሹ።